# የታካሚ መብቶች እና ኃላፊነቶች

**በCorewell Health ለእያንዳንዱ ታካሚ እና ቤተሰብ ልዩ ተሞክሮ ለማቅረብ እንተጋለን። የላቀ ጥራት ያለው እና የግል እንክብካቤ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ ከእርስዎ ጋር በመተባበር እንተጋለን።**

**ታካሚዎች በእንክብካቤ፣ በክብር፣ የግልና ጥራቱን በጠበቀ እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው።**

- በCorewell Health ውስጥ የሚገኙ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ሁሉንም ሰዎች ዘራቸው፣ ቀለማቸው፣ ጾታቸው፣ የጾታ ማንነታቸው እና መገለጫቸው፣ ብሔራዊ መገኛቸው፣ ሀይማኖታቸው፣ ማንነታቸው፣ ሀይማኖታቸው፣ አካል ጉዳተኝነታቸው፣ ዕድሜያቸው፣ HIV በደማቸው መገኘቱ ወይም አለመገኘቱ፣ ጾታቸው፣ የጾታዊ ግንኙነት ፍላጎታቸው፣ ጎሳቸው፣ ወይም ለአገልግሎቶች የሚከፍሉት ክፍያ ምንጮቻቸው ወይም የትኛውም ሌሎች በፌደራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ህግ የተከለከሉ መሰረቶቻቸው ምን ይሁን ምን በአግባቡ መቀበል፣ ክብር መስጠት እና ማገልገል አለባቸው። ታካሚዎች ከጾታ ማንነታቸው ጋር በሚስማማ መልኩ ይስተናገዳሉ።
- እንክብካቤያቸው በሁሉም ጊዜያት በሙያዊና ክብርን በጠበቀ አኳኋን መቅረብ አለበት።
- ታካሚው ውሱን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ያለው ወይም የመስማት እክል ያለበት ከሆነ የምልክትና የቃል ቋንቋ አገልግሎቶች ያለ ክፍያ ይቀርቡለታል።
- እንደ አስፈላጊነቱ ህክምና፣ ሌሎች አገልግሎቶችና ሪፈራል ይቀርባል። የታካሚውን የህክምና ፍላጎቶች ማሟላት ካልቻልን ወደ ሌላ ተቋም እንዲዛወር እናመቻችለን። ሪፈራሎች የሚካሄዱት ማዛወሩ ለምን እንዳስፈለገ ለታካሚው ሙሉ መረጃ ከተሰጠው እና መዛወር ካልፈለገ ሌሎች የህክምና አማራጮች ከቀረቡለት በኋላ ብቻ ነው። ታካሚውን የሚቀበለው ተቋም ዝውውሩን ለመቀበል መስማማት አለበት።
- እንደ አስፈላጊነቱ በታካሚው ካህን፣ ቄስ፣ ራቢ፣ መነኩሴ ወይም ሌላ የሀይማኖት መሪ አማካኝነት ወይም የሚገኝ ከሆነ ደግሞ በCorewell Health የካህን እንክብካቤ አገልግሎት አማካኝነት ለታካሚው የክህነት/መንፈሳዊ እንክብካቤ ለማቅረብ ሁሉም ጥረቶች ይደረጋሉ።
- እንዴት ቅሬታዎችን እንደሚያስመዘግብ እና እንዴት አለመግባባቶችን፣ ክርክሮችን ወይም ግጭቶችን እንደሚፈታ መረጃ የማግኘት። የመረጃ ምንጮችም እንደ የታካሚ ግንኙነቶች፣ የሥነ ምግባር ኮሚቴ እና በህጉ በሚጠየቀው መሰረት ሌሎች ተቆጣጣሪ ድርጅቶች ያሉ አገልግሎቶችን ያካትታሉ።
- እንደ አስፈላጊነቱ የመከላከልና የጥብቅና አገልግሎቶችን መጠቀም መቻል።
- የቤተሰብ አባል ወይም በታካሚው የተመረጠ ተወካይ እና ሀኪሙ ታካሚው ወደ ተቋም ስለመግባቱ በአግባቡ እንዲገለጽላቸው የማድረግ።
- ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የመገናኛ ዘዴዎች እና የኤሌክትሮኒክስና የመረጃ ቴክኖሎጂ እኩል ተደራሽነት አለ።

**ታካሚዎች ስለ ህክምናቸውና የጤና እንክብካቤ ስለሚያደርግላቸው ቡድን የተመለከተ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው።**

ታካሚው የጤና እንክብካቤ ቡድኑ የሚከተሉትን እንዲያቀርብለት ሊጠብቅ ይችላል:

- ስለ ምርመራና ህክምና የተመለከቱ ግልጽ ማብራሪያዎች።
- የህክምናዎች ጥቅሞችና ስጋቶችን ጨምሮ የተወሰኑ ህክምናዎች ወይም ሥነ ሥርዓቶችን የተመለከተ መረጃ እና ለእነዚህ ህክምናዎች በህክምና አሳማኝ የሆኑ አማራጮችን መረጃ።
- ለታካሚዎች እንክብካቤ ኃላፊነት የተሰጠውን ሀኪም ስምና የሙያ ኃላፊነት እና የሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ስምና ኃላፊነት።
- ከሀኪማቸው ወይም ተወካያቸው ያልተጠበቁ ውጤቶችን ጨምሮ የህክምናዎች ውጤቶችን።
- የህክምና መዝገባቸውን የማግኘት። ታካሚው መዝገቡን ከሀኪሙ ወይም ተወካዩ ጋር ሆኖ እንዲያይ ይበረታታል። ታካሚው በተጨማሪም የራሱን የህክምና መዝገብ ቅጂ የመጠየቅ እና በተመጣጣኝ ዋጋ የማግኘት መብት አለው።
- የታካሚው ዝርዝር የህክምና መረጃ ወይም ሌላ የግል የጤና መረጃ ለሶስተኛ ወገኖች የሚሰጠው በታካሚው ሲፈቀድ ብቻ ነው (ለህክምና፣ ክፍያ ወይም ሌሎች የጤና እንክብካቤ ስራዎች በህግ ካልተጠየቀ ወይም ካልተፈቀደ በስተቀር)።

**ታካሚው ስለ እራሱ ህክምና ሰጪ በተመለከተ ውሳኔዎችን የማሳለፍ መብት አለው።**

ታካሚው ወይም የተመደበው ህጋዊ ተወካዩ የሚከተለውን ሊጠብቁ ይችላሉ:

- በታካሚው የጤና እንክብካቤና የእንክብካቤ እቅድ ዝግጅት ላይ ለመሳተፍና ውሳኔዎችን ለማሳለፍ።
- እንደ የታካሚው የደህንነት ስትራቴጂ በታካሚው እንክብካቤ ላይ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ለመበረታታት።
- በህግ እስከሚፈቀደው ድረስ የህክምና እንክብካቤን እና ህክምናን ለመቀበል ወይም ለመቃወም ምርጫ ለማግኘት እና የእነዚህ ውሳኔዎች የህክምና ውጤቶችን ለመስማት።
- የቅድሚያ መመሪያ የመሙላት ዕድል ማግኘት እና መመሪያው በህግ እስከሚፈቀወደው ልክ መተግበሩን ለማወቅ። የሚጠየቅ ከሆነ ሆስፒታሉ እና የእንክብካቤ ቡድኑ ታካሚውን የቅድሚያ መመሪያ እንዲዘጋጅ ሊረዱት ይችላሉ።
- ሌላ ሀኪም በታካሚው ጥያቄና ወጪ ሁለተኛ አስተያየት እንዲሰጥ የማድረግ መብት።
- ከስነ ምግባር ኮሚቴው ምክር ወይም አስተያየት የማግኘት።
- የትኛውም ወይም ሁሉም የቤተሰብ አባላት ወይም ሌሎች በእንክብካቤው ላይ ጉልህ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች እንዲካተቱ ወይም እንዳይካተቱ የመወሰን።
- ስለ ህይወት ዘመን መጨረሻ እንክብካቤ የተመለከተ መረጃ የማግኘት።
- ስለ ክፍያቸው፣ የገንዘብ ድጎማቸው እና የክፍያ አማራጮቻቸው ማብራሪያ የማግኘት። ታካሚዎች በተጨማሪም ከፋያቸው ማንም ይሁን ማን የክፍያቸውን ደረሰኝ ቅጂ የማግኘት መብት አላቸው።

**በግዛት ቁጥጥር የሚደረግባቸው የጤና ወጪ ዕቅዶች የተካተቱ ታካሚዎች በታካሚዎች የሚቺጋን ግዛት ህግ መሰረት ምቾትና ደህንነት የማግኘት መብት አላቸው።**

ታካሚዎች የሚከተሉትን ሊጠብቁ ይችላሉ:

- እንክብካቤን ከጥቃትና ትንኮሳ በጸዳ ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ውጤታማ አካባቢ ለማግኘት። ለድንገተኛ ህክምናዎች የኬሚካል ወይም የአካል ማቀቢያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉት የታካሚውን እና/ወይም ሌሎችን ደህንነት ለመጠበቅ ብቻ ነው።
- ህመማቸው ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲገመገም ለማድረግ እና በህመም መቆጣጠሪያ እቅዶች ላይ ለመሳተፍ።

ታካሚው የሚከተለውን ሊጠብቅ ይችላል:

- ስለ ህመሙና የህመም ማስታገሻ አማራጮቹ የተመለከተ መረጃ ለማግኘት።
- ህመምን ለመከላከል የተመደበ ሃላፊነት የሚሰማው ሰራተኛ።
- ለህመም ሪፖርቶች ፈጣን ምላሽ የሚሰጡ የጤና ባለሙያዎች።

- የታካሚውን ክብር በሚጠብቅ ሁኔታ ውስጥ ግለኝነትን በሚጠብቅ ቦታና ላለባቸው ህመም ተስማሚ የሆኑ አልባሳትን በመልበስ እንክብካቤን ለማግኘት።
- ስለተመከሩ ሥነ ሥርዓቶች ወይም ህክምናዎች በምርመራ ላይ እንደሆኑ የመስማት እና በእንክብካቤያቸው ላይ ተጽእኖ ሳይፈጥሩ እነዚህን ህክምናዎች ያለመቀበል መብት።
- ስማቸውን እና የትውልድ ቀናቸውን በእይታ ምርመራ (ታካሚ ላይ የሚደረግ የመለያ ቁጥር ወይም ሌሎች ሰነዶች) የማረጋገጥ እና የትኛውም ህክምና ወይም ጣልቃገብነት ለታካሚው ከመቅረቡ በፊት የቃል ማረጋገጫ ለማግኘት።
- የደህንነት ስጋቶችን ጨምሮ ስጋቶችን እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉ መረጃ ለማግኘት እና ይህን ያለ በቀል ለማድረግ መበረታታት።

**ታካሚዎች ግላዊነታቸውን እና ሚስጥራቸውን የመከበር መብት አላቸው።**

ታካሚዎች የሚከተሉትን ሊጠብቁ ይችላሉ:

- የግል የህክምና መረጃቸውን ጨምሮ ግላዊነታቸውን ለማስከበር።
- የትኛውም ከሆስፒታሉ ጋር በይፋ ግንኙነት የሌለው ሰውን ያለመቀበል ወይም እንዲያያቸው የማድረግ መብት። ይህ ጠያቂዎችን ወይም ሌሎች እንክብካቤ በማቅረብ ላይ የማይሳተፉ ሰዎችን ይጨምራል።
- ለግል ውይይቶች ስልክ ለመጠቀም።
- አሳማኝ የእይታና የድምጽ ግላዊነትን በሚጠብቅ ቦታ ቃለ መጠይቅ ለመደረግ እና ለመመርመር።
- ጥያቄ ካቀረቡ በምርመራዎች ወይም ሥነ ሥርቶች ወቅት ተመሳሳይ ጾታ ያለው ሰው እንዲገኝ ለማድረግ።
- ለህክምና ዓላማዎች ካልሆነ በስተቀር ልብሳቸውን ላለማውለቅ።
- ማንነትን ከመለየት፣ ምርመራና ህክምና ዓላማዎች ውጭ ለማንኛውም አላማ ለሚደረግ የትኛውም የፊልም ወይም የድምጽ ቀረጻ የጽሁፍ ፍቃድ ለመጠየቅ።

**የታካሚ ኃላፊነቶች**

የሚከተለውን ማድረግ የታካሚ ኃላፊነት ነው:

- የሚከተሉትን ጨምሮ የተሟላ፣ ግልጽና ትክክለኛ የህክምና ታሪክ መረጃ ማቅረብ:
  - የህመምዎ ባህሪ።
  - የቀደሙ ህመሞችና የሆስፒታል ውስጥ አስተኝቶ ህክምናዎች።
  - ልዩ ችግሮች፣ ምልክቶች፣ ህመም ወይም ስጋቶች።
  - የመድሀኒት (የትእዛዝ፣ ያለ ሀኪም ትእዛዝ የሚሰጡ እና የዕጽዋት) አወሳሰድ ታሪክ፣ (መጠን እና ድግግሞሽን ጨምሮ)፣ የመድሀኒቶች አጸፋዊ ምላሾች (ምግብና ላቴክስን ጨምሮ) እና ስጋቶች።
  - የህክምና ሁኔታዎ ለውጦች፣ ሲከሰቱ።
- ስለ ህክምና እቅዱ እና በእቅዱ ላይ ስላልዎ ሚና ካልተገነዘቡ ለመናገር እና ጥያቄዎች ለመጠየቅ።
- ስለ እንክብካቤዎ በተመለከተ በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ።
- በእርስዎ እና በጤና እንክብካቤ ሰጪ ቡድንዎ መካከል የተዘጋጁ ምክረ ሀሳቦችን፣ ምክርና የህክምና ሂደቶችን ለመከተል።
- የሚከተሉትን ጨምሮ ለእንክብካቤ ጥራትና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ለመፍጠር ድጋፍ የሚያደርጉ የCorewell Healthን የታካሚ እንክብካቤና ምግባር ሕጎች ለመከተል፥
  - የሌሎች ታካሚዎችን እና የCorewell Health ሰራተኞችና ንብረት መብቶችን ማክበር።
  - የከትንባሆ ነጻ የሆነ አካባቢ ፖሊሲን ማክበር።
  - ለእንክብካቤዎ ኃላፊነት የተሰጠውን ሀኪም ስም ማወቅ።
- ስለሚቀርበው እንክብካቤ የክፍያ ምንጮች በተመለከተ የተሟላ፣ ትክክለኛና ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለመስጠት እና የመክፈል ግዴታዎችን በወቅቱ ለማሟላት። የሚከተለውን መረጃ በምንሰበስብበት ወቅት የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤ መዘግየት የለበትም።
- ህክምናውን ካልተቀበሉ ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢን መመሪያዎች የማይከተሉ ከሆነ የህክምና ውጤቶችን ለመቀበል እና ኃላፊነት ለመውሰድ።

**ስጋቶች እና ቅሬታዎች**

ስጋት ወይም ቅሬታ ካልዎት ይህን ከእርስዎ ለመስማት ቦታ ከመስጠታችን በተጨማሪ የታካሚ ግንኙነቶች መምሪያን እንዲያነጋግሩ እናበረታታዎታለን። ስጋቶችዎን ተመልክተን ለመፍታት ከእርስዎና ከቤተሰብዎ ጋር አብረን እንሰራለን። ምርጫዎ ከሆነ በተጨማሪም በየትኛውም ጊዜ Michigan ግዛት ወይም የጋራ ኮሚሽን ቅሬታ የማስመዝገብ መብት አልዎት።

የCorewell Health የታካሚ ግንኙነቶች
**844.403.0429**

የግዛቱን ፍቃድ ሰጪ ኤጀንሲ ለማነጋገር:
Licensing and Regulatory Affairs
Bureau of Community and Health Systems
Health Facilities Division
P.O. Box 30664,
Lansing, MI 48909

Michigan ግዛት የቅሬታ ማቅረቢያ የቀጥታ የስልክ ቁጥር፥
**1.800.882.6006**

ለሆስፒታሉ እውቅና የሰጠውን ድርጅት ለማነጋገር።
የጋራ ኮሚሽን
**jointcommission.org**
(በሆም ገጽ ላይ በ"ድርጊት ማዕከል" (Action Center) ውስጥ የሚገኘውን የታካሚ ደህንነት ሁኔታን ሪፖርት ያድርጉ (report a Patient Safety Event) ማስፈንጠሪያን ይጠቀሙ)
በፖስታ:
Office of Quality Monitoring
One Renaissance Boulevard
Oakbrook Terrace, IL 60181
ፋክስ፥ **630.792.5636**

የፍትሀ ብሔር መብቶች ቢሮን ለማነጋገር:
Michigan Department of Civil Rights
350 Ottawa Avenue NE
Grand Rapids, MI 49503
**1.800.482.3604**

Corewell Health © 10.2023